በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን
የልማት ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Development and Inter-Church Aid Commission

Building Bridges of Faith Against Domestic Violence

# የይዘት ማጠቃለያ

# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናት ጋር በቤት ውስጥ ጥቃት ዙሪያ የሚደረግ ዐውደ ጥናት

**ዐውደ ጥናቶቹ በድልድል ፕሮጀክት / Project dldl / የተዘጋጁ ናቸው**

**የፕሮጀክት ተግባሪ፡ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንየልማትና ክርስቲያኒያዊ ተራድኦ ኮሚሽን**

**ሰኔ 2013 ዓ.ም**

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን
የልማት ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Development and Inter-Church Aid Commission

Building Bridges of Faith Against Domestic Violence

## የቅጂ መብት

ከዚህ ፕሮጀክት የሚወጡ  ግኝቶች ሁሉ የታተሙት በ UKRI Open Access ሕግ መሠረት እና ዕውቀትን ለሁሉ ለማካፈል ፕሮጀክቱ ካለበት ግዴታ መነሾ ነው፡፡ ሁሉም ግኝቶች የታተሙት በ Creative Commons Attribution Non Commercial (CC BY-NC 4.0) International Licence, https://creativecommons.org/licenses/by-nc/4.0/ ነው፡፡

## ምስጋና

ይሄ የጽሑፍ ሥራ የተዘጋጀው በዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ ሲሆን የሚከተሉት ግለሰቦች ደግሞ አስተዋጽኦ በማድረግ፣ በመገምገም እና በትርጉም ተሳትፈዋል፡-

1. ወ/ት ሰላማዊት ረታ (የቅ/ሥ/መ/ዩ ምሩቅ) / Ms Selamawit Reta (HTTC graduate)
2. አቶ ኤልያስ ገብረሥላሴ (የቅ/ሥ/መ/ዩ ምሩቅ) / Mr Elias Gebrselassie (HTTC graduate)
3. ወ/ት ትርሲት አጎናፍር / Ms Tirsit Agonafer  (EWLA)
4. መ/ር  አክሊል ዳምጠው / Church Teacher Aklil Damtew (EOC-DICAC)
5. አቶ ባንተአምላክ ገላው  / Mr Banteamlak Gelaw (EOC-DICAC)

በተጨማሪም የሽፋን ገጽ፣ የደብዳቤ አርማ (logo) ስለሠራልን እና የሚታተመውን ስላዘጋጀልን በአዲስ አበባ ለሚገኘው ለ ዲዲኤን የማስታወቂያ ሥራ (DDN Advertising Works) እና ለአቶ ዳንኤል ደስታ (Mr Daniel Desta) ምስጋና እናቀርባለን፡፡

## የማጣቀሻ ጥቆማ

Project dldl/ድልድል (ሰኔ 2013 ዓ.ም) ‹የይዘት ማጠቃለያ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናት ጋር በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ የሚደረግ ዐውደ ጥናት›። Project dldl/ድልድል: Bridging religious studies, gender & development and public health to address domestic violence in religious communities. SOAS University of London.

## ዳራ/ መግቢያ

በኢትዮጵያ አማራ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ሃገረ ስብከት ከኢ/ኦ/ተ/ቤ/ ክርስቲያን ካህናት ጋር የተደረጉት ዐውደ ጥናቶች ዓላማቸው ለካህናት በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ የተሻለ መረዳት እንዲያገኙ ለማገዝ ነው፡፡ ጉዳዮቹም:-

ሀ) በገጠር በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ የጥቃት ዓይነቶችን በተሻለ እንዲገነዘቡ፣

ለ) በአብዛኛው ተጠቂ የሆኑት የሴቶችን እርዳታ የመፈለግ ምልክቶችን እንዲረዱ፣

ሐ) በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ጥቃቶችን አስረጂ የሆኑ የቁሳቁስ፣ ማኅበራዊ-ባሕላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ መለኪያዎችን እንዲለዩ እና በተጨማሪም

መ) በሰሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል በተካሄደው የሥነ-ሰብእ ጥናትና ባሉ ትምህርታዊ መረጃዎች[1] ላይ በመመሥረት የሰዎችን አስተሳሰብ መረዳት እንዲችሉ ናቸው።

**ካህናቱ እያንዳንዱን ዐውደ ጥናት ካጠናቀቁ በኋላ:**

ሀ. ትምህርቶቻቸው እና አባታዊ ምክሮቻቸው ከማኅበራዊ-ባሕላዊ ደንቦች ጋር ተጣምረው በተዘዋዋሪ ጾታን እና ጋብቻን በተመለከተ ያሉትን ግትርና ጎጂ የሆኑ አመለካከቶችን ሊያስቀጥሉ እንደሚችሉና እነዚህ አመለካከቶች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የማይጠቅሙና በጋብቻ ውስጥ ከሚኖር ግጭትና ጥቃት ጋር ሊገናኙ እንደሚችሉ ይረዳሉ።

ለ. ምእመናንን በብቁ ሁኔታ ለማስተማር የሚያስችል የቤተክርስቲያኒቷን የጋብቻ ነገረመለኮታዊ ዕውቀት በማግኘት ጎጂ የሆኑ ልማዶችን መቀየር በሚያስችል መልኩ ማስተማር ይችላሉ።

ሐ. የተጎጂዎችን እና የአጥቂዎችን ሥነ-ልቦና በመረዳት ሁለቱንም በተገቢው መንገድ ለመደገፍ እና ለጋብቻ ውስጥ ጥቃቶች ተጋላጭ የሆኑ ወገኖችን አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ እንዲሸመግሉ(እንዲያስታርቁ) የሚያስችሏቸውን መሣሪያዎች ይታጠቃሉ፣ እና

መ. የድጋፍ ሥርዓቶችን ያውቃሉ፤ ከነዚህ ሥርዓቶች ጋር አብሮ በመሥራት እንዴት ተጎጂዎችን እና አጥቂዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መደገፍ እንደሚችሉም ይረዳሉ።

ሠ. የቤት ውስጥ ጥቃትን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል የተሠሩ ሥራዎች (በዚህ ዐውደ ጥናት መመሪያ አባሪ ውስጥ የተመለከተነውን) እና የኢትዮጵያ ሴቶች የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (EWLA) ምክር በሁለተኛ ክፍል ተጠቃሏል።

ይህ አነስተኛ የሥልጠና መጽሔት ተሳታፊዎች ከሥልጠናው በኋላ ይዘውት የሚሄዱት እና የሚጠቀሙበት ጠቃሚና ቋሚ የሆነ ማጣቀሻ እንዲኖራቸው ለማስቻል ከዐውደ ጥናቱ ገለጻዎች ዋና ዋናውን የሚጠቀልል ነው፡፡ መጽሔቱ የተሰናዳው በዐውደ ጥናቱ በተሸፈኑት ርእሶች እና ጉዳዮች መሠረት ቢሆንም አጠር ለማድረግ ሲባል የተካተቱት አንዳንድ ነጥቦች ቀለል ያሉ ሲሆኑ መንፈሳዊ ድጋፍ በሚሰጡበት ወይም ማኅበረሰቡን በሚያስተምሩበት ወቅት ካህናቱ የራሳቸውን ውሳኔ በመስጠት ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ማሰናሰል ይጠበቅባቸዋል።

## ክፍል አንድ

### በገጠር አከባቢ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም ጥቃትን በተመለከተ የኑሮ ልምዶች እና የሃይማኖት አባቶች ለችግሩ ቀጣይነት ወይም መፍትሄ/ መከላከል/ ያላቸውን ሚና እና የሕይወት ተሞክሯቸውን መረዳት።

ይህ ክፍል በገጠራማው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚያጋጥሙ በጋብቻ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እና የጋብቻ ውስጥ ጥቃት ዓይነቶችን በተመለከተ ገለጻዎችን እና ውይይቶችን አካቷል። ይህ በአክሱም ገጠር በተደረገ ጥናት ላይ የተመሠረተ ነበር። ገለጻው

---

[1] ምርምሩ የተካሄደው እ.ኤ.አ. ከ2008-2009 ዓ.ም. ጥናቱ ሙሉ መጠሪያ:- Istratii, R. "Gender and development through local epistemologies: Understanding conjugal violence among Orthodox *Täwahədo* Christians in northern Ethiopia and implications for changing attitudes and norms within local worldviews." PhD thesis, SOAS University of London, 2019. DOI: https://doi.org/10.25501/SOAS.00030986.

የቤት ውስት ጥቃቶችን፣ የማኅበረሰቡን ሁኔታ እና አባቶች ካህናት እና መምህራን ስለ ጋብቻ እንዴት እንደሚያስተምሩ ይገመግማል። በተጨማሪም ቀሳውስት የጋብቻ ችግር ያለባቸውን እና በትዳር አጋር ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች የሚያቀርቡበትን የኖላዊነት መንገድ ይዳስሳል፤ የእነዚህን መንገዶች ጥንካሬና ድክመትም ይገመግማል።

በኢትዮጵያ የሚኖሩ የተለያዩ ማኅበረሰቦች የቤት ውስጥ ጥቃትን የሚያስተናግዱበት መንገድ በጥቂቱም ቢሆን የተለየ ሊሆን ስለሚችል በአክሱም የተገኘው የጥናት ውጤት ለሁሉም እንደሚሠራ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ነገር ግን በአክሱም የተመዘገቡት አረዳዶች፣ ሁኔታዎች እና ተግባራት በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሲሆን ስለ ችግሩ፣ እንዴት ራሱን እንደሚገልጽ እና እንዴት ተጠብቆ እንደቆየ ብሎም ካህናት አንዳንድ ጎጂ የሆኑ ልማዶችን እንዴት መቀልበስ እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠርም ሊረዱ ይችላሉ። በተጨማሪም የቀረበው ማስረጃ ከ2008-2009 የነበሩ ግኝቶችን የሚያሳይ ሲሆን አሁን ላይ ሁኔታው (በተለይ በትግራይ ባለው ጦርነት) ተቀይሮ ሊሆን ይችላል፡፡

## <u>በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ ጥቃቶችን መረዳት</u>

- የጋብቻ ውስጥ ጭቅጭቅና ጸብ፤ በባሎች መስከር፣ ሌላ ሴት ጋር መሄድ፣ የቤት ወጪን ባለመስጠት ምክንያት የሚፈጠሩ ከርክሮችና አለመግባባቶች።
- በሚስቶችና በባሎች መካከል ያለ ፍትሐዊ ያልሆነ የሥራ ድርሻ ክፍፍል እና በሴቶች ላይ በሚታየው ያለ ዕድሜ ጋብቻ የሚገለጡ ጾታዊ አለመመጣጠኖች።
- ሚስቶች በባሎች መተው (መፈታት) በተለይ ደግሞ ከፍቺ በኋላ ባልየው ለልጅ የሚሆን ቀለብ መቁረጥ ሲሳነው።
- በአጠቃላይ በትዳር ውስጥ ስለሚኖር ግንኙነት (ወሲባዊ ግንኙነት) መገደድ አይወራም። ምክንያቱም ሚስት በማንኛው ጊዜ ከባሏ ጋር የመተኛት ግዴታ እንዳለባት ስለሚጠበቅ ነው (የአባላዘር በሽታ እያለበት ባል ሚስቱን ከእርሱ ጋር እንድትተኛ ከሚያስገድዳት ጊዜ በቀር)።

## <u>ጋብቻ ውስጥ ጥቃቶች ማብራሪያና መንሥኤ</u>

- አብዛኛውን ጊዜ በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጠሩ ጥቃቶች ተጠያቂ የሚሆነው የወንዶች ‹የተፈጥሮ ባሕርይ ሲሆን በጭቅጭቅ ጊዜ ሴቶች ተገዳዳሪ ሆነው ከቀረቡ በተወሰነ ደረጃ ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ።
- እንደ ጥቃቱ ዓይነት ይህ ነገር ከግል ‹የተፈጥሮ ባሕርይ›፣ ከግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እና በማኅበረሰቡ ወስጥ ቀላል የማይባል ቊጥር ባላቸው ሴቶችና ወንዶች አእምሮ ውስጥ ጸንተው ካሉ ያረጁ (ያለፉ) አድሎአዊ አስተሳሰቦች ጋር ሊያያዝ ይችላል።
- አንዳንድ ሴቶች በባሎቻቸው ላይ የሚፈጽሙት ጥቃት ደግሞ ከዘመናዊነት እና የበለጠ ዕኩል ለመሆን ከሚያደርጉት ጥረት ጋር የተዛመዱ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ከአንዳንድ ሴቶች ወንዶች ላይ ከሚያደርሷቸው ጥቃቶች ጋር በማዛመድ አንዳንድ ሴቶች ‹ከባድ› ወይም ‹አስቸጋሪ› ሴቶች ተደርገውይታያሉ።

## <u>የአዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታዎች እና ልማዶች ጥምረት</u>

- በአጠቃላይ በሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች ዘንድ በጋብቻ ውስጥ ያለ ጥቃት በባሕላዊም ይሁን በሃያማኖታዊ መመዘኛዎች ተቀባይነት የለውም።
- ጠንካራ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የሥነ ምግባር መለኪያዎችን እና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ጥቃቶችን የሚኰንኑ ዕሴቶች፡ እርስ በእርስ መረዳዳትን፣ መከባበርና ርቱዕነትን፣ ጥቃትንና ግጭትን ለማቆም የሚደረግ የኀረቤት ጣልቃ ገብነትን እና በድርጊቱ ፈጻሚዎች ላይ በመውቀስና በማሳፈር የሚወሰዱ ቤተ ክህነታዊ ግዝቶችን ይደግፋሉ።

- ነገር ግን በጋብቻ እና በዚህ ዙሪያ ያሉ ግንኙነቶች ላይ ያሉ አስገዳጅነት ያላቸው የሚመስሉ የሚጠበቁ ነገሮች ለምሳሌ ባሎችን እንደ አስተዳዳሪ (ገቢ በማምጣት) እንዲሆኑ እና ሴቷ ቤት ማስተዳደሩ ላይ ሓላፊ እንድትሆን መጠበቅ፣ ሚስት ደግሞ በማንኛውም ጊዜ ለባልየው ወሲባዊ ፍላጎት አዎንታዊ ምላሽ እንድትሰጥ መጠበቅና ሁልጊዜ ጭምት(ሁሌ እሺ ባይ) እንድትሆን መጠበቅ።
- የጋብቻ ውስጥ ጥቃትን በሚመለከት የሚመጡ ክሶችን ፖሊስና የፍርድ ቤት ሰዎች በአግባቡ አለመከታተልን የሚገልጽ በችግሩ ላይ መሥራት ያለባቸው ተቋማት ቸልተኝነት።
- ከአስቸጋሪ የትዳር አጋር ጋር በሚጋፈጡበት ጊዜ በሴቶች ዘንድ ተንሰራፍቶ የሚገኘው መቻል (ችሎ ማለፍ)ና ድብቅነት።

## እምነት በትዳር ውስጥ

- እምነት ለሴቶች ብዙ ጊዜ አቻ የመሆኛ መንገድ ሆኖ ያገለግላል እንጂ እምነቱ ከሚያስተምረው በተቃራኒ የትዳር አጋር ጥቃትን ለማስተባበል ምክንያት ሆኖ የሚቀርብ አይደለም። ነገር ግን አንዳንድ ሴቶች ጥቃት የሚያደርስባቸው ባል ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ የማይወስዱት በእምነታቸው እና ይቅርታ ማድረግ አለብኝ ከሚል አስገዳጅ ስሜት የመነጨ ሊሆን ይችላል።
- ወንዶች ብዙ ጊዜ መንፈሳዊነት ላይ ቀዝቀዝ ያሉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። ግን የአንዳንድ ወንዶች ምስክርነት እንደሚያስረዳው የአንዳንድ ባሎች እምነትን ማእከል ያደረገ አስተሳሰብ እንደ ዝሙት እና ፍቺ ከመሰሉ ብልሹ ጠባያት ይጠብቃል። እንደዚህ ወንዶች ድርጊቶችን የሚከውኑት በካህናቱ በሚነገር ኃጢአትን በሚኰንን ጽድቅን በሚያበረታታ ትርክት አማካኝነት በተፈጠረ እና በሕዝቡ ዘንድ በብዛት ተቀባይነት ባገኘ የሥነ-ምግባር መለኪያ ሥር ነው።

## ችግሩን ስለሚያባብሱ የኃይለኝነት (የሁከት) ባሕርያት መሠረታዊ እምነቶች

- ባጠቃላይ የሰዎች ጨቋኝነትን ከግለሰብ ባሕሪ ጠባይና ከሌሎች ግለሰባዊ ሁኔታዎች ጋር ያያይዙታል እንጂ ከሰፊው የማኅበረሰብ ባሕላዊ ልምድ ወይንም ሥርዓቶች ስሕተት ከመሆን ጋር አይገናኝም። ነገር ግን በትዳር ያለ ጭቆና በሃይማኖትም በባሕልም የተወገዘ ቢሆንም ይህ አስተሳሰብ ችግሩ በድብቅ ተችሎ እንዲታለፍ አድርጓል።
- ሴቶችን ወይንም ሚስቶችን ተገዳዳሪ እንዳይሆኑ የሚገፉ የጾታ መስፈርቶች፣ የወንዶች እምብዛም መንፈሳዊ ያለመሆንና (ሰለዚህም ለክፉ ማኅበረሰባዊ ጫናዎችና ለሰይጣን መንፈስ የተጋለጡ በማድረግ) ባጠቃላይ ማኅበረሰቡ ውስጥ የወንዶችን ያልተገቡ ጸባያትን መቀበል ሴቶች ከጨቋኝ ባሎች ጋር ችለው እንዲኖሩ ሊገፋፉ ይችላሉ።

## ካህናት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና

- ምእመናን በአንዳንድ ቄሶች የትዳር ሕይወት ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች ያስተውላሉ። ሆኖም ግን ለካህናቱ ትምህርቶች ዋጋ ይሰጣሉ። በአጠቃላይም ቄሶች የሚያስተምሩት የእግዚአብሔርን ቃል እንደሆነ ያምናሉ።
- ካህናት በተለምዶ በትዳር ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች እንደ አስታራቂ ሆነው ይታያሉ። በምእመናኑ መካከል ለሚኖሩ ሃይማኖታዊ ነገሮች እንደ ቀዳሚ ማጣቀሻም ይወሰዳሉ።
- አብዛኛዎቹ የገጠር ካህናት የሚጎዱ በባሕልም የተኰነኑ ልምዶችን ይቃወማሉ። ነገር ግን አንዳንዶች ለብሉይ ኪዳኑ የሃይማኖታዊ ወግ አፅንኦት በመስጠት እና የአዲስ ኪዳኑን ሥነ-መለኮታዊ አስተምህሮ ችላ በማለት የሕዝቦችን ተለምዷዊ ወግ የሚያንፀባርቁበት እና የሚያጠናክሩበት ሁኔታ አለ።
- በተጨማሪም ይህን ሁኔታ ካህናት ጠላ መጠጣትን በሚያካትቱ ባሕላዊ ቅርጽ ባላቸው ማኅበሮች ላይ በሚጫወቱት ሚና መገንዘብ ይቻላል።

<u>በጋብቻ ውስጥ የካህናት ሽምግልና</u>

- የጋብቻ ውስጥ ችግሮችን በሚሸመግሉበት ጊዜ ብዙ ካህናት በንቃት ሆነው ሴቷን በደል ደርሶባት እንደሆነ ይጠይቃሉ። ለሽምግልና በተጠሩ ቊጥር ብልሹ ጠባይ ያላቸውን ይገስጻሉ፣ ያልተጠበቁ ውጤቶች ሊኖሯቸው የሚችሉ ሁኔታዎችም እንዲስተካከሉ ይመክራሉ። (በዚህ መጽሔት ሦስተኛው ክፍል ላይ ተዳሷል)
- አጥፊዎቹ አልመለስም ካሉ ካህናቱ ነጻ ፈቃድ መከበር አለበት በሚለው አስተምህሮ መሠረት አያስገድዱም፣ ይተዉታል።
- ካህናት ዘላቂ ትዳር እንዲኖር ቢያሳስቡም ጋብቻ ሰላማዊ መሆን እንዳለበትም ያስተምራሉ። ሁኔታው የማይቀለበስ ከሆነና ሴቷን የሚጎዳ ከሆነ በአጠቃላይ ፍቺንም አይቃወሙም።
- ካህናቱ በትዳር ውስጥ መኖር ስላለበት ሰላም አጽንኦት መስጠታቸውና በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዲችሉ ሚስቶችን መምከራቸው (የባሎች ሚስቶችን መደብደብ ግን አይጨምርም) ሴቶች በትዳር ውስጥ እንዲቆዩ ከሚያደርጉ ማኅበረሰባዊና ቁሳዊ ጫናዎች ጋር ሊደመሩ ይችላሉ።
- ካህናቱ በአብዛኛው ሚስቶች በሚናገሩት ታሪክ ላይ ተመሥርተው ውሳኔ መስጠት አለባቸው። በትዳራቸው ችግር የገጠማቸው ካህናት ግን አንዳንዴ ለባልየው ሊያደሉ ይችላሉ።

<u>**ቁልፍ መልእክቶች**</u>

- በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ሃይማኖታዊ ተግባራት እና ነገረ ሃይማኖት፣ጤናማ ትዳርን እና ፍትሐዊነትና ዕኩልነት የሰፈነበት የጾታ ግንኙነትን ያጠናክራሉ።
- ነገር ግን የሐዲስ ኪዳንን ነገረ መለኮት (ለምሳሌ በዚሁ መጽሔት ላይ የቀረቡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርቶች እንደሚያስረዱት) በዘነጋ በተለምዶ በተያዘ ባሕል ላይ በግትርነት በመቆም እውነተኛው ትውፊትን ከፈጠራ ወጎች መለየት ስለተሳናቸዉ አንዳንድ ምእመናንም ካህናትም ጎጂ የሆኑ ባሕሎች እንዲቀጥሉ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያበርከቱ ይችላሉ።
- የጥቃት ፈጻሚነትን ጠባይ የፈጻሚው ‹ተፈጥሮአዊ ባሕርይ› አድርጎ መመልከት ልማድና እነዚህ ሰዎች ለቅድስና ጠባብ ዕድል ያላቸው ደካማ ሰዎች ናቸው የሚለው እምነት ቤተክርስቲያን ‹እግዚአብሔርን መምሰልን› ገንዘብ እንዴት ማድረግ እንደሚችሉና ራሳቸውን በእግዚአብሔር ተራዳኢነት አሻሽለው ኃጢአተኛና ብልሹ የሆኑ ጠባያትን እንዲያሸንፉ ሊያደርጉ የሚችሉ ትምህርቶችን ማስተማር እንዳለባት ያሳያል።

## ክፍል ሁለት

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ጋብቻ ፣ ፍቺ እና በጋብቻ ውስጥ ስላለ ጥቃት የምታስተምረው ነገረ መለኮታዊ ትምህርት እና ስለ ተመሳሳይ ጉዳይ ቅዱስ ዮሐንስ <u>አፈወርቅ የሚያስተምረው ትምህርት</u>

ይህ ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ጾታዊ ጉዳዮች፣ ጋብቻ እና የቤት ውስጥ ጥቃት የምታስተምረውን ትምህርት ከቀኖና መጻሕፍት እና ከቤተክርስቲያኗ የነገረ መለኮት ሊቃውንት በማጣቀስ የቀረበበት ነው፡፡ በተጨማሪም ስለዚህ ጉዳይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚያስተምራቸው ትምህርቶች እና ካህናትም የመንፈስ ልጆቻቸውን በሚመክሩበት ጊዜ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ወሳኝ ትምህርቶች ቀርቦበታል።

## <u>የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን እና የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትን ታሪካዊ ዕድገት መረዳት</u>

- ❖ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጥንታዊ መሠረት ያላት ናት። መሠረታዊ የሆኑት ዶግማዊ አስተምህሮቶቿ በጊዜ ሂደት በሐዋርያዊ አስተንትኖና ውሳኔ፣ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት፣ በቤተ ክርስቲያን አባቶችና እናቶች ትምህርት ላይ የተመሠረቱና የተብራሩ ናቸው።
- ❖ ከማይቀየሩት ዶግማዊ አስተምህሮዎች ባሻገር ቤተክርስቲያን አዲስ ሁኔታዎችንና ማኅበረሰቦችን በማካተት እምነቱን ከአይሁድ አሻግራ ወደ ግሪክ እና ወደ ኢትዮጵያ ለማስፋፋት ችላለች። አይሁድ ያልሆኑ ሰዎች ወደ እምነት እንዲገቡ ለማስቻል ሐዋርያቱ እራሳቸው በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉትን ጥብቅ ሕጎች (ለምሳሌ የወንዶች ግርዛት) አካተዋል።
- ❖ በአጠቃላይ እምነቱ በታሪክ ኦርቶዶክሳዊ በሆኑ ማኅበረሰቦች ውስጥ በካህናቱና በምእመናኑ ዘንድ በምልዓት ሊተላለፍና ሊኖር የሚገባው ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮን በሚገቱ አንዳንዴም በሚያጨናግፉ የተለያዩ የእምነት መዋቅሮች፣ ፖለቲካዊ ችግሮች እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ ሥር ነው ያደገው (ለምሳሌ በኢትዮጵያ የአሕመድ ግራኝ ወረራ እና የደርግ አገዛዝ።)
- ❖ ስለሆነም ኦርቶዶክሳዊ ካህናትና ምእመናን በእያንዳንዱ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን የተተነተነውና የተኖረው የእምነታቸው ትውፊት ከውጭ ተጽእኖ ነጻ እንዳልነበር መገንዘብ ያስፈልጋል። አንዳንዶቹ ተጽእኖዎች ደግሞ ሰዎች እውነተኛውን ኦርቶዶካሳዊ እምነት ምን እንደሆነ እና እንዴት ሊኖር እንደሚገባ ያላቸውን እውቀት በተወሰነ ደረጃ ሊለውጡና ሊያንሸዋርሩ ይችላሉ።

## <u>የኦርቶዶክሳዊ እምነት ትርጉም</u>

- ❖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከካህናቱም ከምእመናኑም ወገን የሆኑ ሰዎች እምነቱን በሕይወታቸው ውስጥ ከመኖር በሚያዘናጋቸው መልኩ ‹ትክክለኛውን› ወይም ‹እውነተኛውን› እምነት መጠበቅ በሚል ጉዳይ ላይ ተጠምደው ይታያሉ።
- ❖ እምነቱ ሐዋርያትና ቅዱሳን በኖሩበት ኦርቶዶክሳዊ ኅሊና (እሳቤና አመለካከት) ከተያዘና ከተኖረ ትክክል (ኦርቶዶክስ) ነው። የካህናቱ ዓላማ እምነቱን መጠበቅ አይደለም (ይህ የእግዚአብሔር ኃላፊነት ነው።) ይልቁንም ዋናው ኃላፊነታቸው በሕይወታቸው ውስጥ ኦርቶዶክሳዊ ኅሊናን ማጎልበት፣ ደግሞም ምእመናኑን በዚያው ኦርቶክሳዊ ኅሊና በማሰብ እና በመኖር ራሳቸውን አሻሽለውና አሟልተው ድኅነት እንዲያገኙ በእግዚአብሔር የፍቅር ሰዎች እንዲሆኑ መምራት ነው።
- ❖ ይህ ተመሳሳይ የሆነው መልእክትም በትዳር ውስጥ መጉላት አለበት። የካህናት ግዴታ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡና እንዲጾሙ መምከር ብቻ አይደለም። ይልቁንም የትዳር ዓላማው ምን እንደሆነና እንዴት በምልአት መልኩ መኖር እንደሚቻል ለምእመናን መንገርም ጭምር ነው። የትዳር ዓላማው በአንድነት ሆኖ ቅድስናን ማግኘት፣ ትሕትናን መጨመር፣ ራስን ማወቅ እና የትዳር አጋርን በመረዳትና በመቀበል መውደድና ማፍቀር ነው።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ የወንድና የሴት ግንኙነት</u>

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የወንዶችና የሴቶችን ዕኩልነት ትቀበላለች ታስተምራለችም። በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ ያለው ‹ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው› የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ተከታዩን ማብራሪያ ይዟል፡ ‹ወንድ ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡ (ሐተታ) በዚህስ ጊዜ ሔዋን ገና አልተፈጠረችም በኋላ ከታወቀ ብሎ፤ አንድም በእሱ ባሕርይ አለችና እንዲህ አለ።› በዘፍጥረት ትርጓሜ

በሌላም ቦታ ‹እነርሱ› የሚለው በድጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል፡- ‹‹ ‹ዓሣትን የምድርንም አራዊት ግዟቸው› ብሎ አዘዛቸው (እነርሱን)›› እና ‹‹ ‹የሰማይ አእዋፋትን፣ እንስሳትን ሁሉ፣ በዚህ ዓለም የሚመላለሰውን ሁሉ ግዙአቸው› ብሎ ባረካቸው (እነርሱን)።››

## <u>በኢ.ኦ.ተ.ቤ. በጥምቀት ጊዜ የሚስተዋል የጊዜ ልዩነት እና ነገረ መለኮታዊ ማብራሪያው ሥነመለኮታዊ መጽደቅ</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ሥርዓቶች ግን የጾታ ልዩነት የሚስተዋልባቸው ናቸው፤ ለምሳሌ በልጅነት ጥምቀት ሴት ልጅ ወንዶች ከተጠመቁ ከ40 ቀናት በኋላ የምትጠመቅበትን ሥርዓት ማንሣት ይቻላል።

በአንዳንድ የነገረ መለኮት ምሁራን ይሄ ትውፊታዊ ሥርዓት የብሉይ ኪዳን ሥርዓትን የተከተለ እንጂ ሴቶችን ከማሳነስ እሳቤ የመነጨ አይደለም በሚል ይብራራል። ይህ ማብራሪያ እንዳለ ሆኖ ጾታዊ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ የቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓቶች ትኩረቶችን እንድትስብ ያደረገ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኗንም ዘመኑን የዋጀ ምላሽ እንድትሰጥ ግድ የሚል ሆኗል። እንደዚህ ማብራሪያ ከሆነ ግን አዳም ከሔዋን ቀድሞ እንደተፈጠረ እና ሔዋን ከአዳም እንደተገኘች ተጽፏል። ስለዚህም ወንድ ሕፃናት በ 40 ሴት ሕፃናት ደግሞ በ 80 ቀናቸው ይጠመቃሉ።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ ቅዱስ ጋብቻ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋብቻ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ሲሆን ቅድስናውን የጠበቀ እንዲሆን በቤተክርስቲያን በምሥጢረ ቁርባን መፈጸም አለበት።

በእርግጥ ድንግልናቸውን የፈቱና ለሁለተኛ ጊዜ የሚያገቡም በቤተክርስቲያን ማግባት ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ጋብቻዎች በጥብቅ የንስሓ መንገድ የሚከናወኑ ሲሆን የሚፈቀዱትም ከእግዚአብሔር መግቦት አንጻር ዝሙትን ለመከላከል ነው። በዚህ ሂደት መሠረት ጥንዶቹ መጀመርያ የንስሓ አባታቸውን አግኝተው ንስሓ መግባት ሲኖርባቸው የቤተክርስቲያኗን የጋብቻ ሕግጋትም መማር አለባቸው። ጥንዶቹ ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኋላ በካህኑ ለተወሰነው ጊዜ ያህል ይጾማሉ፣ ምጽዋት ይሰጣሉ ወይም ሌሎች ቀኖናዎችን ይቀበላሉ። ከዛ በሌላ ቀን ትዳራቸው የሚታተምበትን ሥጋና ደሙን ለመቀበል አብረው ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ። በዚህ ሁኔታ የሚጸለየው ጸሎትም የተለየ ሲሆን ምሥጢረ ተክሊልም አይፈጸምላቸውም። እንደ ፍትሐ ነገሥት ትእዛዝ ይሄ ጸሎት የፍትሐት ጸሎት የሆነው ፍትሐት ዘወልድ ነው።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ የጋብቻ ዕድሜ</u>

በፍትሐ ነገሥት ትውፊት መሠረት ለአብዛኛዎችሁ ወንዶች የጋብቻ ዕድሜ ከ20 እስከ 25 ሲሆን የሴቶች ደግሞ (እንደ ሃብት ደረጃ) ከ 12 እስከ 15 ነው። **(ፍትሐ ነገሥት፣ 140)** በመጽሐፈ ተክሊል ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የሚከተለውን ትደነግጋለች፤ ‹15 እና ከ15 በላይ የሆነች ድንግል ሴት፤ 18 እና ከ18 በላይ የሆነ ወጣት ድንግል ወንድ› ፤ ድንግልና በሁለቱም ዘንድ መሟላት ያለበት መሥፈርት ነው። **(መጽሐፍ ክስርትና፡ መጽሐፍ ተክሊል፡ መጽሐፍ ቀንዲል፣ 75)**

ነገር ግን አባቶች በአስተምህሮአቸው አዳም የተፈጠረበትን 30 ዓመት በገነት የቆየበትን 7 ዓመት እንዲሁም ሔዋን የተፈጠረችበትን 15 ዓመት መነሻ አድርገው የወንድን የጋብቻ ዕድሜ 37 ዓመት የሴት የጋብቻ ዕድሜ 22 ዓመት ቢሆን

ይመረጣል ይላሉ፡፡ **(የአባቶች አስተምህሮ)** በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግሥት በተለምዶ 15 ዓመት የሆነውን የሴት ልጅ ዕድሜ ሕጋዊ እንዳልሆነና ዝቅተኛው የሴት ልጅ የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት እንደሆነ ይደነግጋል።

ቀሳውስት በቤተክርስቲያን ውስጥም ሆነ በባሕል ውስጥ የሚከናወኑትን ያለዕድሜ ጋብቻዎች መፍቀድ የለባቸውም። ካህናት በአማኞች ቤት ውስጥ የሚካሄዱ ዕድሚያቸው ለጋብቻ ያልደረሱ ሴቶችን የሚያሳትፉ የቃል ኪዳን ሥነ ስርዓቶች ላይ ሲገኙ በእርግጥም ይህንን ልምምድ ያበረታታሉ። ካህናት እንደዚህ ዓይነት ሥነ ሥረዓቶች ላይ መሳተፍ የለባቸውም። ያለዕድሜ ጋብቻም እንዳይፈጸም መገሰጽ አለባቸው።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ የጋብቻ ዓላማዎች</u>

በትውፊት መነጽር የጋብቻ ዓላማዎች ብያኔ ይሄንን ይመስላል፡- (1) የሰው ልጅ ይጠበቅና ይበዛ ዘንድ፣ (2) በባልና በሚስት መካከል የጋርዮሽ መተጋገዝ እንዲኖር እና (3) ጋብቻው ጥንዶቹን ከሥጋ ፍትወት ፈተና ይጠብቃቸዋልና ነው።

ነገር ግን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በተረጎመበት ስብከቶቹ ላይ እንዳብራራው የጋብቻ ዓላማ በብሉይ ኪዳን ጊዜ ከነበረው ልጆችን ከመውለድ ዓላማ አድጎ በሐዲስ ኪዳን ኃጢአተኛ ባሕርይን አስወግዶ በመንፈሳዊ ሕይወት በማደግ ባልና ሚስት በጋራ ሆነው ወደ ቅድስና የሚያድጉበትን ዓላማ ይዟል። ይሄ አረዳድ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትውፊት ውስጥ በበቂ ሁኔታ አልተካተተም ነገር ግን ሕዝቡን በማስተማር ጊዜ አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች በጋብቻ ውስጥ ስላለ አንድነት</u>

በጋብቻ ውስጥ ባል እና ሚስት አንድ ይሆናሉ። ባል የአካሉ ራስ ሲሆን ሚስት ደግሞ የአካሉ አባል ትሆናለች። ነገር ግን ይህ በእርግጥ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት እርስ በእርስ መደጋገፍ ማለት ነው። አንዱ ያለ አንዱ መኖር አይችልም ማለት ነው።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ የጾታ ሚናዎችና እና የሥራ ክፍፍል</u>

ጥብቅ የሆነ ጾታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ጋብቻ የትዳር አጋሮች የሕይወትን ውጣ ውረድ የሚካፈሉበት እና የሚተሳሰቡበት እርስ በእርስ የሚተያዩበት የተቀደሰ ኅብረት ነው።

## <u>የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትምህርቶች ስለ የወንድ ራስነት</u>

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለባል የራስነት ኃላፊነትን ይሰጣል። ነገር ግን ይህ የሚወሰነው ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት እና ራሱን አሳልፎ እንደሰጠላት እርሱም ራሱን ሚስቱን ያለ ምክንያት ለመውደድና ለሚስቱ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለመስጠት ባለው ቁርጠኝነት ነው።

በፍትሐ ነገሥት ባሎች ለሚስቶቻቸው ፍቅር ‹ሊሰጧቸው› እንደሚገባ ሚስቶች ደግሞ ባሎቻቸውን ‹ሊያከብሩ› አእንደሚገባ ጳውሎስ ሥርዓት መሥራቱ ተጠቅሷል። ፍትሐ ነገሥት የቅዱስ ጴጥሮስን የዲድስቅልያ ተግሣጽ ይጠቅሳል፡ ‹የእግዚአብሔር

አገልጋዮች ወንዶች ሆይ ከእናንተ ወገን ወንድ የሚስቱን ችግር ይሸከም ትዕቢተኛ ከዳተኛ አይሁን ቸር ቅን ሚስቱን ደስ ለማሰኘት የሚፋጠን ይሁን እንጂ።› በ ‹ጋብቻ ሥርዓትና ቀኖና› የወንዱ ራስነት የተገለጸው የሚስቱን ደኅንነት በተመለከተ ካለው ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ነው።

<u>**የኢ.ኦ.ተ.ቤ. አስተምህሮ ስለ የትዳር ላይ ጥቃት**</u>

እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ማእከላዊ አስተምህሮ ጋብቻ በጥንዶች መካከል የሚኖር ሰላማዊ አብሮነት ነው።

በፍትሐ ነገሥት ትዳርን ለማፍረስ አንዱ ምክንያት አድርጎ የሚጠቅሰው በጸብ ምክንያት አንዳቸው ጉዳት የደረሰባቸው እንደሆነ መሆኑን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ይሄም ሦስተኛው የትዳር ዓላማ የሆነው በባልና በሚስት መካከል የሚኖር የጋርዮሽ መተጋገዝ ካልተሟላ ነው። ‹(ካለ) ከእነርሱ አንዱ በሌላው ሕይወት ላይ ክፉ ቢያደርግ ነው። ከእነርሱም አንዱ ከሁለተኛው ጋር በመከራከር በውስጡ ሸር ያለበት ክፉ የዓመፅ ሥራ የሚገለጽበት ክርክር ይሆናል (ትዳሩም ይፈርሳል)› ለዚህ ንባብ የተሰጠው የተርጓሚው የህዳግ ማስታወሻ ‹አመፅ› ለሚለው በንባቡ ላይ ላለው ዋና ቃል ጠላትነት የሚለውን ቃል እንደተጠቀመ እና በተጋቢዎቹ ቤተሰቦች መካከል የሚኖር ጠላትነትን እንዳመለከተ ይገልጻል። በተመሳሳይ ክፍል ላይ ዝሙትም እንደተከለከለ ተጠቅሷል፡ ‹ከባልና ከሚስት ባንዱ ወይም ዳግመኛ በዘማዊው ላይ ሞት የሚደርስ ስለሆነ ነው። በቅንአት ምክንያትም ቢሆን ወይም ከሌሎች አመንዝራዎች ለአንዱ አንዱን ያጋባው ዘንድ በሚያበቃ በጋብቻም ቢሆን ወይም በሌሎች።› **(ፍትሐ ነገሥት፣ 149)**

<u>**የኢ.ኦ.ተ.ቤ. አስተምህሮ ስለ ጾታዊ ግንኙነት / ተራክቦ**</u>

‹አንድ አካል ይሆናሉ› ማለት ባልየው ወይም ሚስትየው የትዳር አጋራቸውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርግ/እንድታደርግ ማስገደድ ይችላሉ ማለት አይደለም። ቤተክርስቲያን በትዳር ውስጥ ያለውን የወንዶችን ሥልጣን ለማመጣጠን ባሎች ራሳቸውን እንደ አገልጋይ እንዲመለከቱ ታስተምራለች።

አስገዳጅ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ክርስቲያናዊ ጠባይ ሊታይ አይችልም። እምነቱም ሁሉም ሰው ነጻ እንደሆነና የራሱን ምርጫ ማከናወን እንደሚችል ያስረዳል። ምንም ዓይነት ማስገደድ ክርስቲያናዊ አይደለም። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረን የሰውን ልጅ ግለሰባዊ ማንነት እንደ መገርሰስ ይቆጠራል።

<u>**የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የጋብቻ ትምህርት ላይ የቀረበ ቅኝት**</u>

- ❖ <u>**የወንድ እና ሴት አፈጣጠር ላይ**</u>

በኦሪት ዘፍጥረት ላይ የሰጠውን ትርጓሜ ስንቃኘው ሴቷ ከወንዱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ እና በተመሳሳይ ክብር ሆና መፈጠሯን አጽንኦት ይሰጠዋል። **(ዘፍ ስብከት 3)**

ወንድ እና ሴት አስቀድመው አንድ የመሆናቸውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትም በተደጋጋሚ ያነሣል። **(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ስብከት 20)**

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎችን በተረጎመበት ድርሳኑ ላይም ይህንን ትምህርት ካጸና በኋላ አዳም እንደርሱ ያለች ረዳት እንደተፈጠረችለት ሲያውቅ ‹አጥንቷ ከአጥንቴ› እና ‹ሥጋዋ ከሥጋዬ› ማለቱን ይነግረናል ፡፡ በተጨማሪም የሴት ልጅ ከወንድ መፈጠር ራሱን የቻለ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን እና ይህም ደግሞ አዳም በምንም ሁኔታ ከእርሱ የተለየች ፍጡር እንደሆነች አድርጎ እንዳያያት እንደሆነ ይገልጽልናል። **(ለኤፌሶን ሰዎች ስብከት 20)**

## ❖ <u>*የጋብቻ ዓላማ*</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲያስረዳ ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ ዘርን ማስቀጠል እና ለሰው ልጅ ድኅነት የተዘጋጀው ዕቅድም እንዲፈጸም ማድረግ ተገቢ ነበር ስለዚህም ዘር ማስቀጥል የሚለው ዓላማ ቦታ ተሰጥቶታል።**(በእንተ ድንግልና)**

ሆኖም ግን እግዚአብሔር ትዳርን የሰጠበት ዋነኛው ምክንያት የሰው ልጅ ኃጢያትን እንዳያሸንፍ እንቅፋት የሆኑትን ያልተገቡ ፍላጎቶች ለማስወገድ ነበር። **(በእንተ ድንግልና)**

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን ለማጠየቅ የሚያነሣው ብዙዉን ዘመናቸውን ያለ ልጅ የኖሩትን አብርሃም እና ሳራን ነው፡፡ የአብርሃም እና የሳራ ጋብቻ ለአብርሃም የሚፈልገውን ልጅ የሚያገኝበት መንገድ ሊሆን እንዳልቻለ በመጠቆም፤ ይህም ደግሞ ሰዎች ለመራባት ከፈለጉ ይህንን የሚያደርጉት በራሳቸው ጾታዊ ስሜት በኩል ወይንም በትዳር ስለታቀፉ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ‹ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት› **(በእንተ ድንግልና)**የሚለው ሲታከልበት መሆኑን እንዲገነዘብ አድርጎታል፡፡ በሌላ አገላለጽ ቅዱስ ዮሐንስ እንደሚነግረን ከሆነ እግዚአብሔር ትዳርን ሲሰጥ ዋና ዓላማው ልጅ መውለድ ቢሆን ኖሮ ታላቅ ምሥጢር የሆነውን ትዳር [ተክሊል] መመሥረት ባላስፈለገው ነበር።

## ❖ <u>*ጋብቻ፡- የመዳን ሌላኛው መንገድ*</u>

በኦርቶዶክሳዊ ትውፊት መሠረት፤ ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ ድኅነትን ለማግኘት ሁለት አማራጮች አሉ፡- የመጀመሪያው በድንግልና የምናኔ ሕይወት መኖር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ ነው፡፡ ሁለቱም መንገዶች በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ በተለያዩ ዘመናት እነዚህን መንገዶች ለማጣጣል ከተነሡ መናፍቃን ቤተክርስቲያን ጠብቃናለች።

ቅዱስ ዮሐንስ እንደሚነግረን ከሆነ ጋብቻን መረዳት ያለብን ወንዶች እና ሴቶች ኃጢያትን አሸንፈው ቅድስናን ገንዘብ ሊያደርጉ እንደሚችሉበት ምሥጢር ነው፡፡ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከውድቀት በኋላ በሰው ዘንድ ከፍተኛ ፈተና የሆኑትን እና ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገውን ኅብረትም ከሚከለክሉ ኃጢያቶች፣ ማለትም ከዝሙት እና ገላን ከመቸርቸር ራስን ለመጠበቅ ትዳር ጠቃሚ መሆኑን ትመክራለች።

የትዳርን መንፈሳዊ እና ነገረ ድኅነታዊ ዓላማ መገንዘብና ለምእመናን ማስተማር አስፈላጊ ነው። አብዛኛው በገጠርና በከተማም የሚኖር ሰው ትዳር አብሮ ለመኖር፣ አንድ መኝታ ለመጋራት፣ የሥራ ጫናንን ለመካፈልና ልጆችን ወልዶ ለማሳደግ የሚከወን ማኅበራዊ ውል እንደሆነ ብቻ አድርጎ ይመለከተዋል።

❖ <u>**የቤተሰብ ጣልቃ ገብነትን ስለመቃወም**</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በወንድ እና በሴት መካከል ያለው ኦርቶዶክሳዊ ኅብረት ታላቅ ምሥጢር እንደሆነና ይህም ኅብረት ከእግዚብሔር የተሰጠ መሆኑን ይነግረናል። **(ወደ ቆላስይስ ሰዎች ስብከት 12)**

ወንድ ልጅ ያሳደጉትን አባት እና እናቱን ትቶ ወደማያውቃት ሴት ዘንድ እንዲሄድ መታዘዙ የትዳር ምሥጢር ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ ጠቋሚ አድርጎም ይወስደዋል። **(ወደ ቆላስይስ ሰዎች ስብከት 12)**

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደሚነግረን ከሆነ ባል እና ሚስት በትዳር ከተዋሐዱ በኋላ ሁለት አካል ሳይሆኑ ቀድመው እንደነበሩት አዳም እና ሔዋን ሁሉ አንድ አካል ናቸው። **(ወደ ቆላስይስ ሰዎች ስብከት 20)**

❖ <u>**በእርግጥ ‘መገዛት’ ምን ማለት ነው**</u>

በወንጌል ትርጓሜው ላይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ትዳር ግዴታዎች በዝርዝር ሲያብራራ በዋናነት በቅዱስ ጳውሎስ ‹ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና› በሚለው ትእዛዝ ላይ በመንተራስ ነው። (ኤፌ 5፡22-23) **( (ወደ ኤፌሶን ሰዎች ስብከት 20)**

ከዚህ ጥቅስ በመነሣት ሚስቶች ለባሎቻቸው ልክ ቤተክርስቲያን ራሷ ለሆነው ለክርስቶስ የምታሳየውን ዓይነት ቅዱስ የሆነ ፍራቻና አክብሮት እንዲያሳዩ መጠየቃቸውን (ተጠብቆ ይነበብ) ያብራራል። በኦርቶዶክስ አስተምህሮ ይሄ ፍራቻ ዓለማዊ ከሆነ በዛቻ ከሚመጣ ወይም አንድ ሰው በኃጢአቱ ወይም በጥፋቱ ምክንያት ከሚመጣበት ፍራቻ ፍጹም የተለየ ከፍቅር ጋር ብቻ የተሳሰረ የፍቅር ፍራቻ ነው። የፔንታፖሊሱ (አምስቱ ከተሞች) ሊቅ ኔክታርዮስ እንዳለው ‹ይሄ ፍራቻ እንደ ስሜትነቱ ከፍቅር ጋር የተሳሰረ ሲሆን በሴቷ ነፍስ ውስጥ የባል አክብሮትን የሚፈጥርና ካላቸው ጥብቅ ቁርኝት የተነሣ ባሏን ወደ አለማክበር ደረጃ እንዳትደርስ የሚጠብቃት ነው፡፡› **(እንደ ፔንታፖሊሱ ሜትሮፖሊታን ቅዱስ ኔክታሪዮስ)**

❖ <u>**በእርግጥ የወንድ ራስነት ምን ማለት ነው**</u>

ይሄን ዐሳብ የበለጠ ለማጠንከር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በትዳር ውስጥ የባልን ሓላፊነት ያስረዳበትን በቅርበት (በአጽንኦት) መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

‹ምሳሌውን ገና አልጨረሰምና አሁን ደግሞ ካንተ ምን ሌላ ነገር እንደሚፈልግ ስማ ‹‹ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ›› ብሏልና፡፡(ኤፌ 5፡25-26) ቀደም ብለን በሴቶች በኩል የሚፈለገውን የአክብሮት መጠን አይተናል፤ አሁን ደግሞ ስለ ፍቅር መጠን ስማ፡፡ ልክ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛለት ሚስትህ ላንተ እንድትገዛልህ ትፈልጋለህ? እንግዲያውስ ልክ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን እንደሚያደርገው ሁሉ አንተም ሚስትህን ለመውደድና ለመንከባከብ ሓላፊነቱን መውሰድ አለብህ፡፡ ስለ ሚስትህ ስትል ማንኛውንም ዓይነት ስቃይና መከራ ሞትም ቢሆን ለመቀበል አታቅማማ፡፡ ይሄን ሁሉ አድርገህም ግን ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ያደረገላትን ያክል ለሚስትህ ልታደርግላት አትችልም።› **(ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች፤ ስብከት 18)**

በሌላ አገላለጽ ባል በትዳር ላይ የተሰጠው ራስነት ለሚስቱ ፍቅርና እንክብካቤ ካልሰጠ ሊሟላ አይችልም፡፡ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በእርሱ ዘመን ወንድ የበላይ በሆነበት ማኅበረሰብ ውስጥ እንደነበረው ልማድ ወንድ ይሄን በትዳር ላይ ያለውን የራስነት

ሥልጣን አለአግባብ ጉልበት ለአድማጮቹ ሲያስረዳ ‹ራስ ሰውነትን ያለአግባብ ከቀጣው አብሮ ከሰውነቱ ጋር ይጠፋል›። **(ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች፤ ስብከት 20)**

❖ <u>**የትዳር ላይ ጥቃት**</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በትዳር ውስጥ ያለ ጾታዊ ጥቃትን ያወግዛል፤ ሲያወግዝም ደግሞ ሁለቱንም እንደሚመለከት በመጠቆም ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ሚስቶች ባሎቻቸውን በድህነት ምክንያት እንዳይወቅሱ ወይም እንዳይሰድቡ፤ ባሎችም በሚስቶቻቸው መከበርን በኃይልና በማስፈራራት ሳይሆን በፍቅርና በመልካም ጠባይ ለያገኙት እንደሚገባ መምከሩ ነው።

ይሄም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ **የኤፌሶን መልእክትን** በተረጎመበት ሃያኛ ስብከት ላይ ቀጥሎ በቀረበው መንገድ አጽንኦት ተሰጥቶታል:

‹ባል ይሄንን ሲሰማ ሥልጣን ስላለው (የሚስቱ ራስ ስለሆነ) ሚስቱን መስደብና መጉዳት የለበትም ይልቅስ ለመልካም ነገር ሊያበረታታት ፣ ሊመከራትና ሊያግዛት ይገባል፤ እንደገናም በንግግር ሊያሳምናት እንጂ እጁን ሊያነሣባት አይገባም፡፡ እነዚህ ሁሉ አንድ መንፈሳዊ ከሆነ ሰው መራቅ ያለባቸው ሲሆኑ፤ ከኩራት፣ ከስድብ፣ ከማሸማቀቅና ከማቃለል ይልቅ መምከር፣ ማገዝና መርዳት አለበት።›

‹እንግዲህ አንድ ሰው ባሪያውን ስንኳ በጉልበት መግዛት ካልቻለ የሕይወቱን አጋር ሚስቱን፣ የልጆቹን እናት፣ የደስታውን ምንጭ በጉልበትና በማስፈራራት ሳይሆን በፍቅርና በደስታ ሊያኖራት ይገባል። ሚስት ባልን የምትፈራው ከሆነ ምን ዓይነት ትዳር ይኖራቸዋል? ባልስ እንደባርያ ከሚያኖራትና ነጻነት ከሌላት ሚስቱ ምን ዓይነት ደስታን ሊያገኝ ይችላል? ስለ እርሷ መከራ ቢደርስበት ስንኳ ሊወቅሳት አይገባም ክርስቶስ በቤተክርስቲያን ላይ ይሄን አላደረገምና።›

በተጨማሪም እንዲህ ይላል ‹ሚስት አካልህ ስለሆነች ክፉ ነገሮች የምታደርግባት ከሆነ የራስህን አካል ባለማክበርህ ትዋረዳለህ(ታፍራለህ)› በሌላም ቦታ እንዲሁ ‹የራሱን አካል(ራሱን) የሚጠላ ሰው የለም።› ይላል።

❖ <u>**መለያየት መቼ ይመከራል**</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መፋታትን ላለማበረታታት ይጥራል ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውን ሁለቱን ክፋዮች መለያየት አግባብ አይደለምና። ነገር ግን አብሮነታቸው በሁለቱ መካከል ጠላትነትን እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ ተለያይተው ቢኖሩ ይመርጣል። ይሄን ሲያደርጉ ግን ወደፊት ለመታረቅ በር ይከፍት ዘንድ ሳያገቡ መቆየት እንዳለባቸው ይመከራል። ይሄን የመከረው ግን እርሱ ገንዘብ ካደረገው ኦርቶዶክሳዊ አረዳድ በመነሣት እንጂ ሁሉን የሚገዛ ሕግ ለመሥራት እንዳይደለ መታወቅ አለበት።

‹ላገቡ ሰዎች ክርስቶስ ያዘዘው ነገር ምንድነው? ሚስት ከባሏ እንዳትለይ ከተለየች ግን ሳታገባ እንድትኖር ወይም ከባሏ አንድትታረቅ ነው። በተራክቦ ካለመስማማት እና በሌሎች ተራ ምክንያቶች እንደገናም አንዳቸው ለአንዳቸው ክፉ ከመሆን የተነሣ ትዳሮች ይፈርሳሉ፤ እንዲህ ዓይነት ነገር ባይፈጠር መልካም ነው ከተፈጠረ ግን ሴቷ ሌላ ባል እንዳይኖራት ትዳሩ ፈርሶም ቢሆን በአንድ ቤት አብራው ባትኖርም ስንኳ ባሏን ሳትፈታ ትኑር።› **(ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች፤ ስብከት 19)**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን የልማት ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Development and Inter-Church Aid Commission

Building Bridges of Faith Against Domestic Violence

**<u>መልካም አስተማሪ ማን ነው? ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የምንማረው</u>**

ሀ. ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻን መረዳት እና ማስተማር

ለ.በትኩረት ማዳመጥና በጥንቃቄ መመለስ

ሐ. በራስ የትዳር ሕይወት ለሌሎች አርኣያ መሆን

መ. ውስንነቶችን መረዳትና ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት

**ሀ. <u>ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻን መረዳት እና ማስተማር</u>**

- ካህናት ሌሎችን ለማስተማርና ኦርቶዶክሳዊ በሆነ የትዳር መንገድ ለመምራት ስለ ጋብቻ እና አብሮ በትዳር ስለመኖር ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል።
- ካህናት ለምእመናን በሙሉ ግልጽ የሆኑ ማብራሪያዎችን የማቅረብ፣ ስለትዳር ያለውን ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮ የመተንተን አቅም ሊኖራቸው ይገባል።
- በአሁኑ ጊዜ የሚታዩትን ስለትዳር ዓላማ ያሉ የተዛቡ ግንዛቤዎችን ለማረቅና የተጋቡ ጥንዶች በአንድነት ሆነው ሕይወታቸውን እንዲለውጡ ለማገዝ ካህናት የእግዚአብሔርን ቃል አዘውትረው በአደባባይ እና በግል ደግሞም ለባለትዳሮች ማስተማር አለባቸው።
- ካህናት ከጊዜው ጋር አብሮ እንዴት መሄድ እንደሚቻል፣ በግንኙነት ላይ የሚነሡ አዳዲስ ጥያቄዎችን ለመመለስ፣ በጸሎትና በኦርቶዶክሳዊ ኅሊና በመመራት ስለ ጋብቻ ያለውን አስተምህሮ ከዘመኑ ሁኔታ ጋር እንዴት ማጣጣም ይቻላል የሚለውን መገንዘብ አለባቸው።

**ለ. <u>በትኩረት ማድመጥ እና በማስተዋል መመለስ</u>**

- ካህናት መንፈሳዊ ልጆቻቸውን በትኩረት ማዳመጥ አለባቸው፤ ያላቸውን ጥያቄ፣ ጭንቀትና ፍላጎት በጥንቃቄ ለመረዳት መሞከር አለባቸው። ጋብቻን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ምክር ሲለግሱ (የቤት ውስጥ ጥቃት ችግር በማይሆንበት ሁኔታ) መጀመርያ የቅርብ ጓደኞቻቸውን ማናገር አለባቸው በመቀጠልም ጥንዶቹን ለየብቻ ማናገር እና በመጨረሻም ጥንዶቹ ፈቃደኞች ከሆኑ ሁለቱን አንድ ላይ ማናገር አለባቸው። ስለጉዳዩ ሁለቱም የሚያወሩትን ያለ አድሎ ማዳመጥ አለባቸው።
- ፈራጅ ከመሆን ራሳቸውን መቆጠብ አለባቸው። ይልቁንም ሁለቱን የትዳር አጋሮች በሚያስደስት መልኩ እንዴት ኦርቶዶክሳዊ በሆነ መንገድ የጋብቻ ሕይወታቸውን መምራት እንደሚችሉ በማሳየት መርዳት አለባቸው።
- ካህናት ሰዎች ነገሮችን እንዴት መከወን እደሚችሉ ብቻ ከመንገር ባለፈ ከመንፈሳዊ ልጆቻቸው ጋር መተማመን መፍጠርና ዐሳባቸውንና ጭንቀቶቻቸውን በግልጽ እንዲያካፍሉ ማበረታታት አለባቸው።
- ካህናት ምክርንም በአባታዊ ፍቅርና ጥንቃቄ መስጠት አለባቸው። በጥንዶቹ ላይ በተለይም በጋብቻ ውስጥ ጥቃት የደረሰባቸውን አደጋና ችግር ላይ ሊጥሉ ከሚችሉ ጣልቃ ገብነቶች ራሳቸውን ማቀብ አለባቸው። (በሦስተኛው ክፍል ላይ በጥልቀት የሚብራራ)

ሐ. <u>በራስ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ ጥሩ ምሳሌ መሆን</u>

- ካህናት እንደ ግለሰብና እንደ ባል ለራሳቸው መንፈሳዊ ዕድገት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። እነርሱ ትዳራቸውን ኦርቶዶክሳ በሆነ መንገድ ከመሩ ሌሎች ክርስቲያኖች የእነርሱን ፈለግ ለመከተል ይነሳሳሉ።
- በአጠቃላይ ካህናት እንደ ባልና እንደ ግለሰብ ያለባቸውን ውሱንነት መረዳት ከቻሉ ምእመናን ያሉባቸውን ፈተናዎች ለመረዳት ያግዛቸዋል።
- የጋብቻ ጉዳዮችን በሚመለከቱበት ጊዜ ካህናት በወንድነታቸው ምክንያት ለወንዶች እንዳያዳሉ መጠንቀቅ አለባቸው። በክርስቶስ ጾታን መሠረት ያደረገ ልዩነት የለም። ስለሆነም ካህናት ጾታን መሠረት ያደረገ መድሎን እንዳያደርጉ መጠንቀቅ አለባቸው።

መ. <u>ውስንነቶችን መረዳትና ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት</u>

- ካህናት የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸውንና ችግሮችን በራሳቸው ዐቅም ብቻ መፍታት እንደማይችሉ መረዳት አለባቸው። በሰዎች ልቡና ውስጥ ለውጥን ሊያመጣ የሚችለው ኃይል የእግዚአብሔር ብቻ ነው። ካህናት መንፈሳዊ ልጆቻቸውን ሲመክሩ ሁልጊዜ በጸሎት እየተመሩ መሆን አለበት።
- ካህናት አንዳንድ ጊዜ ትዳር ነክ የሆኑ ነገሮችንና ከበደል ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ በሙያ የተካኑ ሰዎችን ለምሳሌ ማኅበራዊ ሠራተኞችን እና የሥነ ልቡና ባለሙያዎችን እርዳታ ሊጠይቁ እንደሚችሉ መገንዘብ አለባቸው። (በሦስተኛው ክፍል ላይ በጥልቀት የሚብራራ)

## ክፍል ሦስት

### በጋብቻ ውስጥ የጥቃት ሰለባዎችን እና ወንጀለኞችን በአግባቡ የመደገፍ እና የመጠበቅ <u>ሥልጠና</u>

ይሄ ክፍል በኢትዮጵያ ስላለው የሕግ መዋቅር የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው እና በሰሜን ሸዋ የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችን ጉዳይ በመመልከት ዙሪያ ስላለው አሠራር ዕውቀቱ ያላቸው ተሳታፊ ቀሳውስትን ያቀርባል። በተጨማሪም አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይዳስሳል፤ ቀሳውስት ለሥነ አእምሮ ሁኔታቸው እና የገጠሙ ቁስል እንዳይጎዳቸው በመጠንቀቅ ለየቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች፣ ተራፊዎች እና ፈጻሚዎች እንዴት መመለስ እንዳለባቸውም ይዳስሳል።

**<u>በኢትዮጵያ በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ የሕግ ማዕቀፍ</u>**

የድኅረ አብዮቷ ኢትዮጵያ የሴቶችን መብት ለመደንገግና የቅርብ የትዳር አጋር ጥቃትን ወንጀል እንዲሆን ለማድረግ ጠንካራ እርምጃ ወስዳለች።

የመጀመሪያው የፍትሐ ብሔር ሕግ የተመሠረተው የቤተክርስቲያን የቀኖና መጽሐፍ የሆነው ፍትሐ ነገሥት እንደሚያመላክተው በክርስቲያናዊ ዕሴት ላይ ነው።

**በ1960 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሕግ** ላይ የተቀጸለው ድንጋጌ ባልን የቤተሰብ ራስና አስተዳዳሪ እንዲሆን የሚያደርጉ አባታዊ የሆኑ የቤተሰብ ሕጎች በድጋሚ እንዲረቀቁ አድርጓል።

**በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ （1992 ዓ.ም** ላይ የቤተ ዘመድ ሹም የሚለው ሙሉ ለሙሉ ሲሻሻል፤ የቤተ ዘመድ መሪነት የሚለው ደግሞ በዕኩልነት ላይ መሠረት ባደረገ መልኩ ተሻሽሏል።

በተሻሻለው ሕግ ውስጥ የተደነገጉት ሕጎች: (1) በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት ዕኩል መብት አላቸው። (2) ባልና ሚስት በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደኅንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ እና ልጆቻቸው በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነጹ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መተባበር አለባቸው።

**የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት （1987 ዓ.ም）** ‹ሴቶች በበታችነት በመታየታቸው የደረሰባቸው የታሪክ ቅርስ› ተጨማሪ ድጋፍ በማድረግ እንዲስተካከል የሚያስችል ድንጋጌን ይዟል።

አንቀጽ 35 ስለ ‹የሴቶች መብት› የሚናገር ሕግ ነው። ንኡስ አንቀጽ 3 እንዲህ በማለት ያብራራል: ‹በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በዕኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ትኩረት ለመስጠት ነው።›

የሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 35 መንግሥት ሴቶችን የመጠበቅ እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የማስወገድ ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ‹ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም አእምሯቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎች እና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው› ይላል።

**የወንጀል ሕጉ (2004)** ለግለሰቦች እና ለቤተሰብ በተወሰነው መጽሐፍ 5 ውስጥ በጎጂ ድርጊቶች የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በአንድ ክፍል ያጠቃልላል። አንቀፅ 564 እንዲህ ይላል: - ‹ምንም ሰው በትዳር ንደኛው ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት አብሮት በሚኖር ሰው አካል ወይም የእእምሮ ጤንነት ላይ ከባድ ወይም ቀላል ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ጥቃት የፈጸመበት እንደሆነ ተገቢነት ያለው የዚህ ሕግ ድንጋጌ （አንቀጽ ፭፻፶፭ እስከ ፭፻፷） ተፈፃሚ ይሆንበታል።›

በወዳጅነት ወይም በጋብቻ ውስጥ ስለ ወሲባዊ ጥፋቶች ምንም ዓይነት ግልጽ ማጣቀሻ የለም፡፡ ምንም እንኳን ይህ በአንቀጽ 625 ‹አንዲት ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸም ድርጊት› ላይ የተመለከተ ቢመስልም።

አንቀጹም እንዲህ ይነበባል፡- ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ ማንም ሰው ባንዲት ሴት ላይ የደረሰውን ከፍ ያለ ቁሳዊ ችግር ወይም የኅሊና ሀዘን ምክንያት በማድረግ ወይም በጠባቂነት፣ በአስተማሪነት፣ በአሳዳሪነት፣በአሠሪነት ወይም ይህን በመሰለ በማናቸዉም ሌላ ግንኙነት ምክንያት ያገኘዉን ሥልጣን፣ ኃላፊነት ወይም ችሎታ በመጠቀም ከተባለቸዉ ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ። የግል እቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ይቀጣል።

**ኢትዮጵያ የሴቶችን መብቶች በመቀበል ለዓለም አቀፍ ስምምነቶች ትገዛለች።**

**ለምሳሌ፡-**

- በሴቶች ላይ የሚደርሰውን አድልዎ ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት (CEDAW)
- የማፑቶ ፕሮቶኮል፡- በአፍሪካ የሴቶች መብቶች ዙሪያ ለአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝብ መብቶች ቻርተር ፕሮቶኮል
- በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የኃይል ጥቃት የማስወገድ ድንጋጌ (DEVAW)
- የቤጂንግ መድረክ የድርጊት መድረክ፣ በሀገሪቱ ውስጥ የጾታ ዕኩልነትን እና የሴቶችን መብት እንዲስፋፉ የሚያደርግ

## የሃይማኖት አባቶች ሊያውቋቸው የሚገቡ ተጨማሪ የቤት ውስጥ ጥቃት አገልግሎት ተቋማት

- በቀበሌ፣ በወረዳ እና በዞን ደረጃ ያሉ ፖሊስ ጣቢያዎች
- የሴቶች መረዳጃና ዕድገት ኅብረት
- በቀበሌ፣ በወረዳ እና በዞን ደረጃ ያሉ የጤና ቢሮዎች
- በቀበሌ፣ በወረዳ እና በዞን ደረጃ ያሉ የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮዎች
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማት
- የኢትዮጵያ ሴት ጠበቃዎች ኅብረት፡ በኮሚቴ አባላቱ የተወከሉት የሴቶች የፖሊስ መኮንኖች፣ የመንግሥስት አቃቤ ሕጎች እና ሌሎች ታዋቂ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ያቀፉ ሲሆን ይህም ለሴቶች ነፃ የሕግ ምክር ለመስጠት ይረዳል። አገልግሎቱ ለማንኛውም ዓይነት ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሴቶች ወይም ለማንኛውም የሕግ ጉዳዮች (ሲቪል ወይም የወንጀል) ጠበቆች እና ደጋፊዎችን መሾምን ያጠቃልላል።
- ተስፋ ብርሃን እና ሕፃናት መርጃ ድርጀት፡ ሥልጠናዎችን መስጠት፣ የጤና ትምህርት እንዲሁም ሴቶችን በተለያዩ ቡድኖች በማደራጀት በተለያዩ የራስ አገዝ እንቅስቃሴዎች እና የማኅልበት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።
- የደብረ ብርሃን ዩንቨርሲቲ የሕግ ክፍል፡ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን ብቻውን ወይም ከሌሎች ቢሮዎች እና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሰጣል።
- የሴቶች ቡና ጠጡ ፕሮግራም:- ሴቶች በማንኛውም ጉዳይ ላይ መወያየት የሚችሉበት፣ አዲስ ትምህርት የሚያገኙበት እና ልምዶችን የሚጋሩበት ማኅበረሰብን መሠረት ያደረገ የሴቶች ስብስብ

## የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችንና አድራሾችን የሰለባዎችን ደኅንነት በሚያስጠብቅ መልኩ እንዴት እንርዳቸው?

የተደራጀ፣ ሀገር አቀፍ ባለ ድርሻ አካላት ባሏቸው ባደጉ ሀገራት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ቀሳውስት የአጥቂነት ጠባይ በሚገጥማቸው ጊዜ ጥቃት የተፈጸመበትን ግለሰብ ደኅንነት በማስቀደም አጥቂውንም ተጠቂውንም ወደ ተገቢው አገልግሎት ሰጪ አካል መላክ አለባቸው እንጂ ችግሩን ‹ለመፍታት› (መፍትሄ ሊያደርጉ) መሞከር የለባቸውም። በሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከሰተውን የቤት ውስጥ ጥቃትን ለመቅረፍ የሚሰሩ ባለሙያዎች (ስፔሻሊስቶች) የሃይማኖት አባቶች ለተጎጂው ሁኔታ ልዩ ትኩረት ሊሰጡ እንደሚገባ እና ታሪኩን ሲያዳምጡ ተጎጂው የተጠቂነት ስሜቱ እንዳያይል መረዳታቸውን የሚያሳዩ ምልክቶችን በመስጠት መስማት እንዳለባቸው ይመክራ። ከዚህም በላይ ቀሳውስት ጥቃት አድራሹን ሰው ለ‹ማረቅ› መሞከር የለባቸው ምክንያቱም እንዲቆጣ እና በተጠቂው ግለሰብ ላይ ወይም በራሱ በቁሱ ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወስድ ሊያደርገው ይችላል።

ይህ መጠለያ ወይም የሴቶች ጠበቆች ማኅበራት ፈጣን ድጋፍ ለመስጠት ሁል ጊዜ በማይገኙበት ወይም እንደ ፖሊስ ጣቢያ ያሉ ተቋማት የቤት ውስጥ ጥቃቶችን ለመፍታት እምብዛም ውጤታማ በማይሆኑባቸው በኢትዮጵያ የገጠር ኅብረተሰብ ውስጥ ሁሌ የሚቻል አይደለም። በተጨማሪም ቀሳውስት በተጋቢዎች ሕይወት ውስጥ እንደ መንፈሳዊ አባት (የነፍስ አባቶች) በሚጫወቱት ማዕከላዊ ሚና ምክንያት መንፈሳዊ ልጆችን የሚመክሩ ካህናት እና መነኮሳት የትዳር ውስጥ ግጭት ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እንዲያስታርቁ ብዙውን ጊዜ በመጀመሪያ ለሽምግልና የሚጠሩ ናቸው እነርሱም ለዚህ እምቢተኛ አይደሉም። የሃይማኖት አባቶች ከሁለቱም ወገኖች በመመርመር፣ ችግሩን ለመረዳት በመሞከር እና የጥፋተኛውን ጎጂ ጠባይ ለመለወጥ ግዝት በመጣል የማሸማገል ዝንባሌ አላቸው።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ የሃይማኖት አባቶች ተጎጂዎች እራሳቸውን የሚያገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ለመገንዘብ እና የተጠቂው ስጋት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም አለባቸው። ለተጎጂው ወገን ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋዎች ለመቀነስ የችግሩን አጣዳፊነት እና የተጎጂውን እና አጥቂውን ሥነ-ልቦና ሁኔታ በመረዳት መንፈሳዊ ፣ ቁሳዊ ወይም ሌላ ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

## የጥቃት አድራሾችን ሥነ ልቡና መረዳት

- ወንድ ጥቃት አድራሾች (በማኅበረሰቡ ውስጥ ብዙውን ቍጥር የሚይዙ ስለሆነ) በተለይ አካላዊ ጥቃት ያደረሱ ከሆነ በቀላሉ ለመናደድ ቅርብ ሊሆኑ ስለሚችሉ ስሜታቸው እና ንዴታቸውን የመቆጣጠር ዐቅም ላይኖራቸው ይችላል። ጥቃት አድራሾች ከባለቤታቸው ወይም ከሌሎች ለሚመጣ የፍርድ ቃላት ስስ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ጥቃት አድራሾችን በቀጥታ ማነጋገርጥያቄዎችን በመጠየቃቸው ምክንያት የተገመቱና ማስፈራሪያ የደረሰባቸው ስለሚመስላቸው ወይም ባለቤታቸው ችግሩን ለሌላ ሰው በመናገሯ ምክንያት በበቀል ስሜት ሆነው በባለቤታቸው ወይም ሊያሸማግል በገባ ሦስተኛ ወገን ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ።
- ብዙ ጊዜ ጥቃት አድራሾች  ለመጥፎ ጠባያቸው ሓላፊነት መውሰድ አይፈልጉም። ብዙ ጊዜ ደግሞ በሦስተኛ ወገን የሚነሡ ችግሮችን አሳንሰው ይመለከታሉ።

## የጥቃት ሰለባዎችን ሥነ ልቡና መረዳት

- ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች (በማኅበረሰቡ ውስጥ ብዙውን ቍጥር የሚይዙ ስለሆነ) ብዙ ጊዜ የደረሰባቸውን መከራ አያካፍሉም። ከካህናት ጋር ከተገናኙም ችግሩን አቅልለው ይናገራሉ። (ለምሳሌ፡- ጥቃት እንዳልሆነ በመናገር ይልቁንም ባልየው ‹አስቸጋሪ›፣ ‹ከባድ› ወይም ‹ተከራካሪ› በመሆኑ ምክንያት የደረሰ ችግር መሆኑን ይናገራሉ።)
- በትዳር አጋር ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ለጠየቁት እርዳታ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ድብርት፣ ከፍተኛ ጭንቀት እና ሥነ ልቡናዊ ምልክቶች ለምሳሌ ከከባድ ጉዳት በኋላ የሚመጡ የጭንቀትና የመታወክ ምልክቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቃል።

## የትዳር ውስጥ ጥቃቶችን እንዴት እናሸማግል?

- ከቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችና አድራሾች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ፣ እነዚህን የሥነ ልቡና ሁኔታዎችና ዝንባሌዎች በጥንቃቄ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
- በጥቃት ተጸዕኖ የደረሰባቸው ጥንዶች የነፍስ አባት የሆኑ ወይም እንዲያሸማግሉ የተጠሩ ካህናት የጥቃት ሰለባዎችንም ሆነ አድራሾችን ጫና ውስጥ ከቶ የሰለባዎችን ጉዳት፣ የአድራሾችን ደግሞ በደል በማያጎላ መልኩ እንዴት ድጋፍ መስጠት እንደሚችሉ ማሰብ አለባቸው።
- ካህናት ተጎጂዎች የደረሰባቸውን መከራ የመደበቅ ዝንባሌ፣ የጎጂዎች ደግሞ ላደረሱት ጥፋት ኃላፊነት ያለመውሰድ ወይም ጥፋቱን የማሳነስ ዝንባሌዎች ላይ ጠንቃቃ እና ንቁ መሆን አለባቸው።

## ተጎጂው የትዳር አጋር ጥቃትን በሚያመለክትበት ጊዜ ልንወስዳቸው የሚገቡ ተጨባጭ ደረጃዎች(ቅደም ተከተሎች)

ሀ. ያለችበትን የአደጋ እና የጉዳት መጠን ለማወቅ ተጎጂዋን በጥንቃቄና በመረዳት ማነጋገር።

ለ. ወደ ጥቃት የወሰድውን መንገድ ምንም ይሁን ምንም ዓይነት ጥቃት በእምነት ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለውና በምንም መልኩ መታሰብ ስንኳ እንደሌለበት ለተጎጂዋ አስረግጦ መናገር።

ሐ. ተጎጂዋ ምን እንደምትፈልግ መጠየቅ ምክር እፈልጋለው ካለች ከዚህ በፊት የዘረዘርናቸው አገልግሎቶችን መንገርና ተጎጂዋን ይህንን መረጃ በወረቀት እንዳትጽፈው ማስጠንቀቅ ምክንያቱም በአጥፊው ሰው መረጃው ሊገኝ ስለሚችልና ወደ ብስጭት ወስዷቸው ለበቀል ሊያነሣሣቸው ስለሚችል።

መ. በራሳቸው ወደ ፖሊስ፣ ጤና እና ሌሎች አገልግሎቶ ሰጪዎች ሄዶ እርዳታ ለማግኘት ካመነቱ አብረው በጋራ ለመሄድ ፈቃደኛነትን ማሳየት። አብሮ መታየት ትክክል ያልሆነ ነገር መኖሩን እንዳይሸፍንና ከተለመደው ነገር ውጪ እንዳይመስል እርግጠኛ መሆን።

<u>**አጥፊውን ሰው የምንቀርብበት ተጨባጭ ደረጃዎች**</u>

ሀ. ከጥፋተኛው ሰው ጋር ስለ ጥፋቱ በቀጥታ ከመነጋገር መቆጠብ። ይልቁንም ምንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ተጎጂውን ማማከር። ተጎጂው እየተጋፈጠ ያለውን የአደጋ መጠን እና አጥፊው ሰው በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ እንዴት ለነገሮች መልስ እንደሚሰጥ የበለጠ ያውቃል።

ለ. ተጎጂው ሽምግልና ከፈለገና በጊዜው ምንም የሚያሰጋ የበቀል ስሜት ከሌለ፣ ለጥፋተኛው ሰው ስለችግሩ ያለውን የመረዳት መጠንና ስለሚያሳየው ጸባይ ያለውን የተጠያቂነት መንፈስ ማነጋገርና መንፈሳዊ ምክሮችን መስጠትጥ።

ሐ. ጥቃቱ የተገለጠ ከሆነና ተጎጂው ለደረሰበት ጉዳት ተገቢውን ግብረ-መልስ ከሰጠ፣ አጥፊውን ሰው ስላደረገው ነገርና ፈቃደኛ ከሆነ ደግሞ ጠባዩን ለማረቅ የሚጠቅሙትን ነገሮች በቅደም ተከተል ምክር መስጠጥ።(አሁን ባለው ሁኔታ የካህናት ተለምዷዊ አሰራር ነው።)

መ. በማኅበሩ ውስጥ አጥፊዎች እንዳሉ ከታወቀ፣ ተከታታይነት ያለው ስብከትን(አጥፊውን በማይነጥል መልኩ) ማለትም ባል ለሚስቱ ሊኖረው የሚገባውን ራስን መሥዋዕት የማድረግ ሥነ ልቡናን፣ ጥቃት ኢ-ኦርቶዶክሳዊ ጠባይ እንደሆነ መስበክና ባሎች ለሚስቶች “ርቱዕ/ጻድቅ”እንዲሆኑ እና የአመጸኝነት ጠባይ ከሚያመጣቸው ኃጢአቶች እንዲሸሽ ማበረታታት።

## <u>ዋና ዋና መልእክቶች</u>

- ❖ ካህናት የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸውንና ችግሮችን በራሳቸው ዐቅም ብቻ መፍታት እንደማይችሉ መረዳት አለባቸው። በሰዎች ልቡና ውስጥ ለውጥን ሊያመጣ የሚችለው ኃይል የእግዚአብሔር ብቻ ነው። ካህናት መንፈሳዊ ልጆቻቸውን ሲመከሩ ሁልጊዜ በጸሎት እየተመሩ መሆን አለበት።
- ❖ ካህናት አንዳንድ ጊዜ ትዳር ነክ የሆኑ ነገሮችንና ከበደል ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሙያ የተካኑ ሰዎችን ለምሳሌ ማኅበራዊ ሠራተኞችን እና የሥነ ልቡና ባለሙያዎችን እርዳታ ሊጠይቁ እንደሚችሉ መገንዘብ።